# ለ አርሊንግተን ዴሞክራቶች ድህረ-ገጽ የሚሆን ትርጉም

## አስፈላጊ ቀናት እና ድምጽ መስጠትን የተመለከተ መረጃ

ድምጽዎን ለዴሞክራቶች ይስጡ- ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 5

አስቀድሞ ድምጽ መስጫ ቀን- ዓርብ፣ ሴፕቴምበር 20- ቅዳሜም ኖቬምበር 2

- በአካል ቀርቦ አስቀድሞ ድምጽ መስጠትን በተመለከተ የድምጽ መስጫ ሰዓታት እና ቦታን የተመለከተ ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎን https://vote.arlingtonva.gov/Early-Voting ን ይጎብኙ።

ድምጽ ለመስጠት ለመመዝገብ ወይም ምዝገባዎን ለማደስ የመጨረሻው ቀን - ማክሰኞ፣ ኦክተበር 15

- ድምጽ ለመስጠት ለመመዝገብ፣ እባክዎን https://vote.elections.virginia.gov/VoterInformation ን ይጎብኙ

በፖስታ የሚላክ ድምጽ መስጫ ለመጠየቅ የመጨረሻው ቀን- ዓርብ፣ ኦክተበር 25 እስከ 5pm (ከሰዓት)

- በፖስታ ድምጽ መስጫ ለመጠየቅ፣ እባክዎን https://vote.elections.virginia.gov/VoterInformation ን በመጎብኘት፣ “Apply to Vote Absentee by Mail” የሚለውን ይምረጡ

የፖስታ ድምጽ መስጫ የመመለሻ የመጨረሻው ቀን - ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 5

- የድምጽ መስጫዎን ወደ 24/7 ክፍት ወደ ሆነው የድምጽ መስጫ ማጠራቀሚያ ሳጥን፣ ወደ በስራ ሰአታት አስቀድሞ ድምጽ መስጫ ወደ ሆነው ቦታ ወይም በምርጫው ቀን እስከ 7pm (ከሰዓት) ወደ ማንኛውም የድምጽ መስጫ ቦታ በመሄድ ይመልሱ።

- የድምጽ መስጫዎች በፖስታ የሚላኩ ከሆነ፣ እስከ ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 5 ድረስ የፖስታ ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል። ይሁን እንጂ፣ የድምጽ መስጫዎ ቀኑን ጠብቆ እንዲደርሰን፣ እስከ ሰኞ፣ ኦክቶበር 28 ድረስ እንዲልኩት እናበረታታለን።

የምርጫ ቀን፣ ኖቬምበር 5, 2024, 6:00am (ጠዋት)- 7:00pm (ከሰዓት)

- እሰከ መጨረሻው የምዝገባ ቀን ድረስ ድምጽ ለመስጠት ያልተመዘገቡ ከሆነ፣ በምርጫው ቀን ድምጽ ለመስጠት መመዝገብ ይችላሉ። በተለመደው የድምጽ መስጫ ጣብያዎ ላይ ወይም ወደ አስቀድሞ ድምጽ መስጫ ቦታ በመምጣት ግዜያዊ ድምጽ መስጫዎን ተጠቅመው ድምጽ

መስጠት ይችላሉ። በምርጫው ቀን የሚሄዱበት የድምጽ መስጫ ቦታ ለማወቅ፣ እባክዎን https://vote.arlingtonva.gov/Voter-Registration/Same-Day-Registration ን ይጎብኙ

## 2024 የዴሞክራቲክ ፓርቲ ዕጩዎች

## ፕሬዚደንት/ምክትል ፕሬዚደንት

**Kamala Harris**

ድህረ-ገጽ

ማህበራዊ ሚድያ

- Facebook
- Instagram
- X

ግለ ታሪክ

Kamala Harris ለፍትሕ፣ ለእኩልነት እና ለሰብአዊ መብቶች ትግል ለማካሄድ ቁርጠኛ የሆኑ ፈር ቀዳጅ መሪ ናቸው። ምክትል ፕሬዚደንት ሆነው በሚያገለግሉበት ግዜ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ የጤና እንክብካቤ፣ ፍትሃዊ የሆነ ደመወዝ እና የአከባቢ ንብረት ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ደግፈው የሰሩ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ዴሞክራሲን ለማሳደግ የሚያስችሉ ዓለም አቀፋዊ ትብብሮች እንዲኖሩ የሰሩ ናቸው። በሴኔቱም ውስጥ፣ የምርጫ ደህንነት፣ ተደራሽ የሆነ የጤና እንክብካቤ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድል እንዲኖር ድጋፍ ሰጥተው ሲሰሩ ቆይተዋል። የካሊፎርኒያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ሆነው በሚሰሩበትም ግዜ፣ ዳግመኛ በወንጀል ስራ ላይ መሳተፍን ለመቀነስ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን የደገፉ፣ የቤት ባለቤቶች እና ተማሪዎች የህግ ጥበቃ እንዲኖራቸው ያደረጉ እና ለጋብቻ እኩልነት የታገሉ ናቸው። እንደ አንድ ኩሩ የ Howard University እና የ UC Hastings ምሩቅ፣ Harris የመጀመሪያዋ ሴት፣ ጥቁር አሜሪካዊ እና ደቡብ ኤዢያዊ አሜሪካዊ ምክትል ፕሬዚደንት በመሆን መሰናክሎችን የሰባበሩ ናቸው። የ አዲሱን ትውልድ መሪዎች ይበልጥ ፍትሃዊ እና እኩልነት ያለበት ማህበረሰብ እንዲኖር በማድረግ ላይ እንዲሰሩ የማነቃቃት የእናቷን Dr. Shyamala Gopalan Harris ሌጋሲ አስቀጥላለች። በማያወላውል ቁርጠኝነት እና በማያቋርጥ ጥልቅ ስሜት፣ Harris ለሁሉም አሜሪካውያን ብሩህ የወደፊት ጊዜ ለመፍጠር ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ይሰራሉ።

**Tim Walz**

ድህረ-ገጽ
ማህበራዊ ሚድያ

- Facebook
- Instagram
- X

<u>ግለ ታሪክ</u>

ገዢ Tim Walz የአሜሪካን ሰራተኛ ቤተሰቦች ለማገልገል በህይወታቸው ሙሉ ሲሰሩ ቆይተዋል። ዕድሜ ልክ ሚድዌስተርን የሆኑት Walz፣ በ 17 አመታቸው በወታደራዊ ብሄራዊ ጥበቃ ለመሰተፍ ተመዝግበው፣ ለ 24 አመታትን በማገልገል እንደ ኮማንድ ሳጅን ሜጀር ሆነው ጡረታ ወጥተዋል። ኮሌጅ ገብቶ ትምህርት ለመማር GI Bill የተጠቀሙ ሲሆን፣ ከዚህም በመቀጠል የሁለተኛ ደረጃ አስተማሪ እና የእግር ኳስ አሰልጣኝ በመሆን ቡድናቸውን የመጀመሪያውን የግዛት አቀፍ ዋንጫ እንዲያመጣ መርተውታል። Walz ለገበሬዎች፣ አርበኞች እና የገጠር ማሕበረሰቦች መብት ተሟጋች በመሆን የሚኒሶታን የኮንግረስ ዲስትሪክትን ወግ አጥባቂ የሆነ ቦታን በመወከል ነው ወደ ፖለቲካው የገቡት። እንደ አንድ ገዢ፣ Walz ለ መካከለኛውን መደብ ጥቅም የሚሰጡ፣ እንደ ግብር ቅነሳ፣ የኢንሱሊን ዋጋ መቀነስ፣ እና ከደሞዝ ጋር የሚኖር የቤተሰብ ዕረፍትን የመሳሰሉ ፖሊሲዎችን ሲደግፉ የነበሩ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ፣ ለ ህዝባዊ ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት፣ በፖሊስ ላይ መዋእለ ነዋያቸውን በማፍሰስ እና የጦር መሳሪያ ሽያጭ በተመለከተ ዓለም አቀፍ የሆኑ የድህረ ታሪክ ምርመራዎች ስራ ላይ እንዲውሉ አድርገዋል። የስነ ተዋልዶ መብቶች ጠንካራ ተሟጋች የሆኑት Walz፣ የውርጃ መብትን የሚደግፍ የህግ ማዕቀፍ የፈረሙ ናቸው። ገዥ Walz እና ባለቤታቸው Gwen በጋራ ሁለት ልጆች ያፈሩ ሲሆን፣ ለሁሉም አሜሪካውያን የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተደራሽ መሆኑ ለማረጋገጥ ጥልቅ ቁርጠኝነት የሚጋሩም ናቸው።

## ሴናተር/ ተወካይ

**<u>Tim Kaine</u>**

ድህረ-ገጽ
ማህበራዊ ሚድያ

- Facebook
- Instagram
- X

<u>ግለ ታሪክ</u>

በ ሪችሞንድ የሲቪል መብቶች ጠበቃ ሆነው ሲሰሩ ከነበረበት  እስከ የ ዩኤስ የቨርጂንያ ሴናተር ሆኖ እስከሰሩበት ግዜ ድረስ፣ ህይወቱን ሌሎችን ለመርዳት እና ለ ቨርጂንያ ነዋሪዎች መብት ጥብቅና በመቆም ነው ያሳለፉት። Tim በተመጣጣኝ ክፍያ የሚቀርብ የጤና እንክብካቤ ለሁሉም አሜሪካውያን ያለውን ተደራሽነት በማስፋፋት፣ የመከላከያ አባላት ባለቤቶችን ስራ አጥነት በመቀነስ፣ ለአከባቢያችን የህግ

አስከባሪ አካላትን የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ እና በማዘኛ የሚሰጡ መድሃኒቶችን ዋጋ በመቀነስ ዙርያ ትልልቅ ድሎችን የተቀዳጁ ናቸው። Tim ታማኝ ባል እና አባት ናቸው። ከቤተሰብ እና ከጓደኞቻቸው ጋር ጊዜ ማሳለፍ፣ የእግር ጉዞ ማድረግ፣ ካምፕ ሰርቶ መስክ ላይ ግዜ ማሳለፍ፣ ታንኳ መቅዘፍ፣ብስክሌት መንዳት፣ ማንበብ እና  ዜማዎችን በማዳመጥም ሆነ በኮመንዌልዝ ማህበረሰብ ውስጥ ካሉ ቡድኖች ጋር ሃርሞኒካን በመጫወት ለሙዚቃ ያለውን ፍቅር መለማመድ ያስደስታቸዋል።

**Don Beyer**

ድህረ-ገጽ

ማህበራዊ ሚድያ

- Facebook
- Instagram
- X

ግለ ታሪክ

የኮንግረስ አባል የሆኑት Don Beyer፣ ፣ አርሊንገተን፣ አሌክሳንደሪያ፣ ፎልስ ቸርች እና የፌርፋክስ ካውንቲን የተወሰነ ክፍል በመወከል በ ዩኤስ የ ቨርጂንያን 8ኛውን ዲስትሪክት ተወካይ በመሆን ለ አምስተኛ ግዜ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። በ ኮንግረሱ የጋራ የኢኮኖሚ ኮሚቴ ውስጥ ከፍተኛ የዴሞክራት ተወካይ ናቸው፣ ወሳኝ በሆነው House Committee on Ways and Means ውስጥም በማገልገል ላይ ይገኛሉ። የ New Democrat Coalition’s Climate Change (አዲሱ የዴሞክትራት ትብብር ለከባቢ አየር ለውጥ) ግብረ ሃይል እና የ Congressional Progressive Caucus አባል ናቸው። የ Congressional Fusion Caucus መስራችም ናቸው።

## የካውንቲ ቦርድ

**Julius D. “JD” Spain, Sr.**

ድህረ-ገጽ

ማህበራዊ ሚድያ

- Facebook
- Instagram
- X
- YouTube

ግለ ታሪክ

Julius D. “JD” Spain, Sr., አባት፣ተጋይ አርበኛ እና የማህበረሰብ እንደዚሁም የንግድ መሪ ናቸው። በ ዩኤስ የባህር ሃይል ውስጥ ለ 26 ዓመታት በኩራት ያገለገሉ ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ በ ኢራቅ የውግያ ግንባሮች፣ በ NATO የቤልጂየም ዋና ቢሮ ላይም ዲፕሎማሲ ስራ ላይ፣ እንደዚሁም እንደ ኮንግረስ ምሁር

ሆነውም ስራዎችን ሰርተዋል። JD የሀገራችን ከፈተኛ ከሚባሉት የሰራዊት የክብር ሽልማቶች ውስጥ የ Legion of Merit ተሸላሚም ናቸው። ዛሬ ላይ፣JD ከፈተኛ የንግድ አማካሪ ሲሆኑ፣ በ George Mason University President's Innovation and Inclusive Excellence Councils(ጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት የፈጠራ እና አካታችነት የልህቀት ምክር ቤቶች) ውስጥ በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

J.D. የጉልምስና ህይወታቸውን ለህዝብ አገልግሎት ያዋሉ ናቸው። በ አርሊንግተን ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተሾሙ፣ እና ሁለት ጊዜ የ NAACP አርሊንግተን ቅርንጫፍ ፕሬዝዳንት ሆነው የተመረጡ እንደዚሁም በደርዘን ለሚቆጠሩ ለትርፍ ባልተቋቋሙ ድርጅቶች ላይ እና ችግሮችን በመፍታት ላይ በጎ ፈቃደኛ ሆነው አገልግለዋል።

JD እና 31 ዓመቷ ባለቤታቸው Adriana፣ በ አርሊንገተን ፔንሮዝ የመኖሪያ ሰፈር ውስጥ ከ 2009 ጀምረው በመኖር ላይ ይገኛሉ። የሶስት የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤት ተመራቂዎች ወላጆች እና የሶስት አመት የልጅ ልጅ አያቶችም ናቸው።

# የትምህርት ቤት ቦርድ

**Kathleen Clark**

ድህረ-ገጽ

ማህበራዊ ሚድያ

- Facebook
- Instagram
- X

ግለ ታሪክ

Kathleen Clark ኩሩ የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች [APS] ተመራቂ ናቸው። እሳቸው እና ባለቤታቸው ዶሚንየን ሂልስ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን፣ በ APS (9ኛ፣ 7ኛ እና 3ኛ ክፍል) ተማሪዎች የሆኑ ሶስት ልጆችም አሏቸው።

Kathleen ቁርጠኛ የማህበረሰብ መሪ እና የሙብት ተሟጋች ሲሆኑ፣ በ APS ውስጥ  ስርዓታዊ መሻሻሎች እንዲካሄዱ በመታገል ላይ ናቸው። ባለፉት 6 ዓመታት ውስጥ የስትራቴጂክ እቅድ አስተባባሪ ኮሚቴ ምክትል ሊቀመንበር በመሆን እና በ ልዩ ትምህርት PTA እና ዶሚኒየን ሂልስ ሲቪክ ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ አገልግለዋል። በሞያቸው Kathleen ፣ ለአስራ ስድስት የ Gap Inc. የውስጥ ኦዲተር ሆነው ሰርተዋል፣ በዚህም፣ የተገዢነት ኦዲት፣ ከጫፍ እስከ ጫፍ ያሉትን ድርጅታዊ ሂደቶች መገምገም እና አደጋን እና በድርጅቱ ላይ ሊኖረው ስለሚችለው ተጽእኖ የመገምገም ስራዎችን ሰርተዋል።  Parents@GapInc Equality & Belonging Group ውስጥ ተባባሪ ሊቀመንበር በመሆን ያገለገሉ ሲሆን፣ በዚህም ውስጥ ተንከባካቢዎችን ከፕሮግራም እና ግብዓቶች ጋር የማገናኘት ስራዎችን ሰርተዋል። የ Kathleen ሂደቶችን፣ በጀቶችን እና ስርአታዊ አስተዳደርን የመገምገም ብቃት እና ካላቸው ርህራሄ፣ አመራር እና የማህበረሰብ ግንባታ ልምድ ጋር ተደምሮ፣ እንደ አንድ የት/ቤት የቦርድ አባል በትክክል የታሰበበት ውሳኔ በመወሰን ላይ ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል።

**Zuraya Tapia-Hadley**

ድህረ-ገጽ

ማህበራዊ ሚድያ

- Facebook
- Instagram

ግለ ታሪክ

የሁለት የAPS ተማሪዎች እናት እና የ20 አመት የአርሊንግተን ነዋሪ የሆኑት Zuraya Tapia-Hadley የተማሪዎችን እና ወላጆችን ፍላጎት እና ከ አስተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና አስተዳዳሪዎች ጋር በቅርበት የመተባበርን አስፈላጊነት ይረዳሉ። ይህ ትብብር ላይ መሰረት ያደረገ አካሄዳቸው፣ Arlington Education Association (የአርሊንግተን ትምህርት ማህበር)፣ educator's union (የአስተማሪ ማህበር)፣ NoVA Labor (የኖቪኤ ሰራተኛ) እና Sierra Club (የሴራ ክለብ) ድጋፍ አስገኝቶላቸዋል።

ለብዙ አሥርት ዓመታት በበጎ ፈቃደኝነት የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረጋቸው እና እንደ ጠበቃ፣ ተሟጋች እና የህዝብ ጉዳይ ባለሙያ ሆነው በሰሩት ስራ፣ በዋና ዋና ኮርፖሬሽኖች እና ብሄራዊ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የፖሊሲ እና የግንኙነት ጉዳዮችን የሚፈትኑ ፈጠራዊ የሆኑ መፍትሄዎችን ለማዘጋጀት አስችሏቸዋል።

የ Zuraya ካላቸው የህይወት ልምድ ጋር፣ በህግ እና በሞያዊ ጥብቅና የካበተ ልምድ እንደዚሁም በ አካባቢ፣ በግዛት እና በአገር አቀፍ ደረጃ ያላቸው የጥብቅና ልምድ ጋር ተደምሮ፣ APS ለእያንዳንዱ ልጅ ከሁሉም የበለጠና እና ፍትሃዊ እና ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲሰጥ ለማስቻል ይረዳዋል።

የ Zuraya ራዕይ እና ልምድ በሁሉም አሁን ላይ በአርሊንግተን የሚገኙ የግዛት እና አከባቢ ተመራጮች ዘንድ እና በብዙ ከዚህ በፊት ተመርጠው የነበሩ መሪዎች፣ለምሳሌ Walter Tejada፣ Emma Violand-Sanchez፣Monique O'Grady፣ እና Barbara Kanninen ድጋፍ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል።